# የህዳሴው ግድብ የሰላም ፕሮጀክት ነው !!

ዮናስ 12/23/13

የበርካታ ትላልቅና አለም አቀፍ ወንዞች ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ሃይል በማመንጨት በኩል ያለችበት ደረጃ ገና የሚባል ብቻ ሳይሆን ያልተነካ እና ፈቅም ያላለ ነው፡፡ የአባይ ባለቤትነታችንን በመርሳት ዓባይን አትንኩብኝ ከምትለው ግብጽ አንፃር ስንለካ ደግሞ በርግጥም ያለንበት ደረጃ የሚያሳዝን ነው፡፡ ዛሬ ላይ በረሃይቱ ግብጽ 27 ሽህ ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ስታመነጭ የወንዞች ምንጭና መነሃሪያ የሆነችው ኢትዮጵያ ግን ገና ከ2 ሺህ ሜጋ ዋት ብዙም ፈቅ ሳትል ትገኛለች፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰአት ሁኔታዎች በመለወጥ ላይ ይገኛሉ። የታላቁ አባይ ባለቤት እንደመሆናችን መጠን ትሩፋቱን ከማንም በላይ ልንጠቀም ግድ የሚለን ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ ደረጃው ቢለያየም የተፋሰሱ ሃገራትም ከአባይ የመጠቀም መብታቸውም እንዲሁ የተጠበቀና ማንም ሊቸራቸውና ሊነሣቸው የማይገባ መሆኑ በስፋት ሲወሳ የነበረ ጉዳይ ነው፡፡

የዘመናት ቁጭታችን ስለሆነው አባይ ለዘመናት ስናዜም፣ ስንዘፍን፣ ስንተርትና ክራር ስንከረክር የመቆየታችን ታሪክ በህዳሴው ግድብ በመሰረታዊነት ሊቀየር እነሆ መንገዱን ከግማሽ በላይ ብንሄድም ዓባይ መለኮታዊ ስጦታዬ ነው ስታል ለዘመናት የፎከረችው ግብጽ ዛሬም ሃሣቧን የቀየረች አይመስልም፡፡ ይልቁንም ጠዋትና ማታ የተምታቱ ሃሣቦችንና ህጋዊ መሠረት የሌላቸውን ጥያቄዎች በማንሣት የቀድሞ ገገሯን ትምክህት በመድገም ላይ ትገኛለች፡፡ በአባይ ላይ አንዳች ነገር እንዳንሠራ ላለፉት በርካታ አመታት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንቅፋትነቷን በተግባር ያሳየች ከመሆኑም በላይ፤ በተለይም ካለንበት ድህነት አኳያ የውጭ  የፋይናንስ ምንጮቻችን ላይ ተነግሮ በማያልቅ ውትወታዋ የታሠቡ ፕሮጀክቶቻችንን ሁሉ ለማጨናገፍ ያላደረገችው ሙከራ የለም፡፡ የኛን ጉዳይ በዚህ መንገድ ዘግታ ሌሎቹን የተፋሰስ አገራት በተለይም ልትገዳደራት እንደምትችል በሠጋቻት ሱዳን ላይ የተለያዩ የልማት መደለያ ፕሮጀክቶችን በመገንባት አፏን ልታዘጋ ብትሞክርም ገሚሡ "በጭቡ ጌታ" ሲወድም ገሚሡም እየተባባሰ የመጣውን

የሱዳናውያን የልማት ጥያቄ ሊያስተነፍሰው ባለመቻሉ የድለላው መንገድ አሁን የተዘጋና መቋጫውን ያገኘ ይመስላል፡፡

ግብጽ፣ በአለም አቀፉ ብቻ ሳይሆን በራሷ የውሃ ፕሮፌሰሮቿ ጭምር በአባይ ውሃ አጠቃቀም ላይ የምትከተለው መንገድ እንደማያዋጣት እና ዘላቂነት እንደማይኖረው ምክር ቢሠጣትም፤ ይልቁንም የተከተላቸው የድለላ መንገድ የትም የማያደርስና እንደሃገር የሚጠቅማት የጋራ ልማት ስትራቴጂ (Collective development Strategy) እንደሆነ፤ መንገዱም ማንም አሸናፊ ማንም ተሸናፊ የማይሆንበት እንደሆነ የተነገራትን አልሠማ ማለቷ ዛሬ ላይ የደለለቻቸውም ሆኑ አትለግሱ ያለቻቸው ሃገራት ፊታቸውን ያዞሩባት ዘንድ ግድ ብሏቸዋል፡፡

የትኛውም ሃገር ከሃገራት ጋር በሚኖረው ግንኙነት መነሻው የራሱን ጥቅም ማስጠበቅ መሆኑ የፖለቲካ ሀሁ ነው፡፡ ስለሆነም የተፋሰሱ ሃገራት በሙሉ ከድህነት ለመውጣት በሚያደርጉት ጥረትና ዘላቂነት ላለው ልማት ከግብጽ ምጽዋት ይልቅ የሚያዋጣቸው ተፈጥሮ በቸራቸው ሃብት መጠቀም መሆኑ ግድና የጊዜ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። እነሆ ጊዜው ደርሶ  አባይን በራሳችን አቅም መገንባት የምንችልበት ደረጃ ላይ መድረሳችንና አለም አቀፍ ስትራቴጂያዊ መዳረሻ መሆናችን  በሠንበት ላይ ደብረዘይት እንዲሉ አበው ለኢትዮጵያችን ህዳሴ ለህዳሴው ግድብ ያበቃን ከመሆንም አልፎ በህዳሴያችን በፈጠርነው አቅም ወዳጅ ሃገራትን ማብዛት ችለን ግብጽ ላይ ፊት እንዲዞር ለማስችል አበቃን፡፡ ግድቡ ለተፋሰሱ ሃገራት ሁሉ የተሻለ ጠቀሜታ . . . በተለይም ለግብጽና ሱዳን የላቀና ዘለቄታዊነት ያለው ፋይዳ እንዳለው በማስገንዘብ በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲፈጠርና ግድቡም የሠላም ፕሮጀክት እንደሚሆን በተግባርም ሆነ በወረቀት ሃገራችን ለአለም እያረጋገጠች ነው፡፡

ይህ ትክክል መሆኑ የገባችውና ካለ ትብብርም አባይን ማልማት የማይሞከር መሆኑን የተረዱት ወገኖች በእኩል ተጠቃሚነት ላይ ያልተመሰረተ የውሀ አጠቃቀም ወደ አልተፈለገ ግጭት ሊወስድ እንደሚችል የተገነዘቡት ሃገራት የትብብር ማእቀፉን በመፈረምና በየፓርላማዎቻቸው በማጽደቅ ቁርጠኝነታቸውን ሲያረጋግጡ እሜቴ ግብጽ ግን የራሷን ወኪሎች ጨምሮ አለም አቀፍ ባለሙያዎች የተሣተፉበትን የጥናት ውጤት ለመቀበል ያቅራት ይመስላል፡፡ "የልዩነታችን  መቋጫ አለም አቀፉ የባለሙያዎች የጥናት ወረቀት ነው" ስትል የከረመችው ግብጽ አተገባበሩን በተመለከተ በተጠራው ስብሰባ ላይ

ከትግበራው በፊት ሌላ ጥናት ዳግሞ በመጠየቅ ባረጀውና ባፈጀው ኃላቀር መንገዷ ለመጓዝ የቆረጠች የሚመስል ፍርደ-ገምድል ሃሣቧን ገልጻለች፡፡ በአንፃሩ የሱዳኑ አልበሽር ከኢትዮጵያ ጋር በጋራ ለመስራት ያላቸውን ቁርጠኝነትና ግብጽንም ወደዚሁ እና ጠቃሚ ወደሆነው መስመር እንድትገባ ለመደገፍ ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ መሆናቸውን ከቃልም ባለፈ በተግባር የሚያረጋግጡ ስለመሆናቸው ለአለማቀፉ ህብረተሰብ ይፋ አድርገዋል፡፡

ለግብጽ ያረጀና ያፈጀ የልዩነት አስተሳሰብ ቀደም ብሎ እንኳ ሊያዋጣት የሚያስችል ፍንጭ እያገኘችበት ይሆናል ብለን ልንገምት እንችላለን፡፡ የአሁኑ ግን የጅል ይሁን የሞኝ የህዳሴው ባይታወቅም፣ ግድቡ ያለበትን ደረጃ እያየች ወደኋላ ለመመለስ ማሠቧ የሚገርም ነው፡፡ ለምን የሚለውን ለማብራራት ለሶስት ዓመት ጥቂት ጉዳይ የሆነውን የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ግንባታ ወቅታዊ ሁኔታ በጥቂቱ ማየት ተገቢና የግብጽን ቅዠት እንዲሁም የሱዳንን መንቃት ከመሰረቱ ለመገንዘብ ያስችለናል፡፡

"እኛው ግንበኛ፣ እኛው የፋይናንስ ምንጭ፣ እኛው መሃንዲሶች፣ . . . ሆነን እንሠራዋለን" በማለት ታላቁና ባለራእዩ መሪ መለስ ዜናዊ የታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ መሠረት ካኖሩበት ሠዓት ጀምሮ የአባይ ቁጭት ሲያንገበግበው የነበረው መላው ኢትዮጵያዊ እስካሁንም የዘለቀውንና ወደፊትም እንደሚቀጥል የማያጠራጥረውን ድጋፉን በገንዘብም፣ በጉልበትም ሆነ በሙያው እየደገፈ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ መሬት ላይ ያለውን የግንባታ ሥራ ሥንቃኝ 6500 የሚሆኑ ሠራተኞች 1700 በሚደርሱ ማሽኖች ቀን ከሌት በመስራት ያን የቁጭት ዘመን እየታደጉት ነው፡፡ በዚሁ ነሰረት፣ በዋናው ግድብ አካባቢ አጠቃላይ የቁፋርው መጠን 6 ሚሊዮን 271 ሽህ 458 ሜትር ኪዩብ እንደደረሰ የሚጠቁሙት ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሣትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት የተገኙት መረጃዎች፤ የሁሉም የሃይል ማመንጫ ቤቶች ግንባታ የቁፋሮ ሥራ እንደቀጠለና ግድቡ ሙሉ ለሙሉ ከመጠናቀቁ በፊት ሃይል የሚያመነጩ ዩኒቶች አካባቢ የቁፋሮው ሥራም 480 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ እንደደረሰ ያመለክታሉ፡፡ በተለይ ግድቡ ግብጽ አብዝታ የተንጨረጨረችበትን የወንዙን ተፈጥሯዊ አቅጣጫ የማስቀየስ ሥራ ከተከናወነ በኃላ፤ የውሃው መጠን ሲበዛ እንደማስተንፈሻ እንዲከፈቱና እንዲዘጉ ሆነው የሚያገለግሉ ግዙፍ የሆኑ አራት የብረት አሸንዳዎች (Box Culvert) በመገንባት ላይ ናቸው። የአርማታ ሙሌቱን ለማከናወን የሚያስችሉ (Convey Belt) የተቦካውን አርማታ የሚያጓጉዝ መስመሮች ዝርጋታ ተጠናቋል፡፡ ግድቡ የሚያርፍበት አሥተማማኝ ቦታ

ለማግኘትም በሚደረግ የከርሠ ምድር ፍተሻ በቀን ቢያንስ ሁለት ጊዜ ያህል የድማሚት ፍንዳታዎችም እየተደረጉ ነው፡፡

ቁፋሮአቸው በተጠናቀቁ አንዳንድ የግድቡ ክፍሎች ላይ የአርማታ ሙሌት ሥራ እየተከናወነ ሲሆን ከአርማታ ሙሌቱ ጐን ለጐንም የብረታ ብረት ተከላ (Hydraulic Steel Structure) ሥራም እየተሰራ ነው። የሰራተኛ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ በአብዛኛው በተጠናቀቀበት በዚህ ስፍራ ከግድቡ በስተቀኝና በስተግራ በኩል በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ቶን አርማታ (ኮንክሪት) ማምረት የሚችሉ ፋብሪካዎች እየተገነቡ ሲሆን በስተቀኝ በኩል ያለው ፋብሪካ ተጠናቆም ስራ መጀመሩን ከምክር ቤቱ የተገኙ መረጃዎች ያረጋግጣሉ። የግድቡን ዘላቂነት ያለው አገልግሎት ማረጋገጥ እንዲያስችልና ግድቡ በደለል ተሞልቶ የውሃው መጠን ለግድቡም ሆነ ለተፋሰሱ ሃገራት እንዳይቀንስ በ2004-2005 ዓ/ም 7.7 ቢሊዮን የሚደርሱ ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኞችን በ4.8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ አርሶ አደሩ ተክሎ በመንከባከብ ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ሁለት ዓመታት ብቻ በ19 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት ላይ 28 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች የተፈጥሮ ሃብት ልማትና የጥበቃ ስራ አከናውነዋል።

እነዚህና ሌሎች ያልተጠቀሱ በርካታ ግንባታዎችና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች በተጨባጭ መሬት ላይ እየታዩ ባለበት ሁኔታና ጊዜ፤ በአናቱም ግድቡ ለተፋሰሱ ሃገራት ዘላቂ ጥቅም እንጂ ስጋት እንዳልሆነ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች እየተናገሩና ጥናታቸውንም ይፋ እያደረጉ ባለበት ሁኔታና ጊዜ፤ ከ200 በላይ የሚሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ባሉባት ዓለማችን የውሃ ዲፕሎማሲና የአያያዝ ተሞክሮ ባልጠፋበት ሁኔታና ጊዜ፤ የግብፅ "ለኔ ብቻ" መርህ አሁንም ለምንም ትርፍ ቢባል ተገቢ ያልሆነና የማያዋጣ ነው። ዳሩ ግን በውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ምክንያት፣ በፖለቲካዊም ይሁን በፋይናንሳዊ ምክንያት ግብጽን ተጠግተውና ለግብጽ አስተሳሰብ ተገዝተው የነበሩት ሱዳናውያኑ በአባይ ላይ ከመጠቀም አልፎ በአባይ ውሃ ሙላት ጊዜ ይደርስባቸው የነበረውን መጥለቅለቅና በደለል ጠረጋ የሚወጣ ወጪ እንዴት ማዳን እንደሚቻል ከተከዜው ግድብ ተምረው በአልበሽር በኩል በትብብር፣ ስለጋራ ልማትና ስለጋራ ጥቅም እጃቸውን ወደላይ አንስተዋል።

ግብጽ ይህ ይግረመኝ ብላ ሳታበቃና የነአልበሽርን ትምህርት ለመጋራት ሳትሻ፣ እነሆ ከሰሞኑ ደግሞ የኢትዮጵያን የሃይል ምንጭ ፍላጎትና አቅም እንዲሁም ተከታታይነት ያላቸው የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ግንባታ ስራዎች የተመለከተ ጥናት ይፋ መሆኑም፤

ምናልባት የግብጽ አይነ ልቦና ላይ ብርሃንን ይፈነጥቅ እና ወደቀልቧ ይመልሳት እንደሆነ የሚጠበቅ እና የምናየው ሲሆን፤ የሃገራችንም ሆነ የህዝቦቿ ምኞት ኧረ ምን እኛ ብቻ፣ የተፋሰሱ ሃገራትም ምኞት ግብጽ ወደቀልቧ እንድትመለስና ማንም አሸናፊ ማንም ተሸናፊ ወደማይሆንበት የትብብር ካምፕ እንድትቀላቀል ነው።

የግብጽን ቀልብ ሊገዛ እንደሚችል የምንጠብቀው የ25 ዓመታት መሪ የሃይል ዘርፍን ጥናትና እቅድ ያስጠናው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን ጥናቱን ለውይይት ይፋ ባደረገበት ወቅት እንደተገለፀው ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ 20 እና 25 ዓመታት 24 የውሃ ሃይል ማመንጫ ግድቦችን የምትሰራ ሲሆን 15ቱ በአባይ ተፋሰስ ላይ የሚገነቡ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ናቸው። እነዚህ ግድቦችም በግብጽ ላይ አንዳች ጉዳት እንደማይኖራቸው ጥናቱ ያረጋገጠ ሲሆን ግድቦቹም 1700 ሜጋ ዋት በላኛው መንደያ፣ 1600 ሜጋ ዋት ካራዶቦ፣ ላኛውና ታችኛው ዳቡስ፣ ያዳ አንድና ሁለት፣ አለልቱ ምስራቅና ምእራብ እንዲሁም ታችኛው ደዴሳ አካባቢ እንደሚገኙ ጥናቱ አመልክቷል። ኢትዮጵያ እስከ 2037 (እ.ኤ.አ) ድረስ ከ300-1200 ሜጋ ዋት የኒውክለር ሃይል ለማመንጨት እንደተዘጋጀችና እቅዱም እንዳላት በጥናቱ ይፋ ሆኗል። ይህ ደግሞ ለግብጽም ሆነ ለሌሎች የተፋሰሱም ሆነ አጠቃላይ አፍሪካ ህይወት እንጂ ሊያስከትለው የሚችል ምንም አይነት አደጋ እንደማይሆን ሊሰመርበትና አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል።

ባጠቃላይ፣ ግብጽም ሆነች ሌሎች ልዩነት ያላቸው ወገኖች እንዲማሩ መክረን ታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ የተመለከተው የኢትዮጵያና የህዝቦቿ አቋም ግን ያው ትብብርን የተመለከተውና ማንም አሸናፊ ማንም ተሸናፊ የማይሆንበት ( Win Win Approach)፣ ይህም የማይለወጥና በጽኑ መሰረት ላይ ያረፈ መሆኑን አሁንም እንናገራለን። ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሃገራዊ መግባባት ፈጥሮ የሁሉንም ህዝብ አሻራ በማኖር እየተገነባ ያለ የባንዲራ ፕሮጀክት እንደሆነ እንዲታወቅልን እንሻለን፤ የህዳሴው ግደብ በዚህ ዘመን የተገኘ የሃገራችንና የህዝቦቿ ታላቅ ስጦታም እደሆነ እንዲታወቅልን እንሻለን። የህዳሴው ግደብ በዚህ ዘመን የተገኘ የሃገራችንና የህዝቦቿ ታላቅ ስጦታም እንደሆነ እንዲታወቅልን እንፈልጋለን። ይህ ብቻ አይደለም፣ የህዳሴው ግድብ እንደ አድዋ ድል እስከወዲያኛው ለትውልድ የሚዘከር እና የኢትዮጵያውያን ቋሚ ሃውልት እንደሆነም እንዲታወቅልን ደግመን ደጋግመን እናረጋግጣለን። በጥናትም ሆነ በተግባር ግድቡ ለታችኛው ተፋሰስ ሃገራት ጉዳት እንደሌለው የተረጋገጠ በመሆኑም ፕሮጀክቱ ሃይል

የማመንጫ ብቻ ሳይሆን የሰላም ፕሮጀክት እንደሆነም መላው አለም እንዲያውቅልንም ሆነ አውቆ እንዲያሳውቅልን ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንናገራለን።